# በኪንግ ካውንቲ ሀይቅ ዳርቻዎች አዲስ የመዝጊያ እና የመከፈቻ ደንቦች የማህበረሰብ ጤናን በተሻለ ሁኔታ ይከላከላሉ

የበጋው ወቅት ሊጀምር ገና አንድ ወር ቢቀረውም ኪንግ ካውንቲ በዚህ ሳምንት በታዋቂ ሀይቅ ዳርቻዎች (የቋንቋ አማራጮችን ያገኛሉ) የውሃ ጥራትን መከታተል ጀምሯል። ይህ ዓመታዊ መርሃ ግብር በዋና ወቅት የማህበረሰቡን ጤና ለመጠበቅ ይረዳል።

ይህን የምናደርገው ከግንቦት አጋማሽ እስከ መስከረም አጋማሽ ባለው ጊዜ ውስጥ ከሁለት ደርዘን በላይ በሆኑ የባህር ዳርቻዎች የውሃውን ጥራት በመከታተል ነው። የተፈጥሮ ሃብት እና ፓርኮች መምሪያ፣ የኪንግ ካውንቲ የአካባቢ ቤተ ሙከራ እና በካውንቲ ውስጥ ያሉ ከተሞች ሁሉም ከማህበረሰብ ጤና ጋር አጋርነት አላቸው።

የአካባቢ ሳይንቲስቶች በዋና ወቅት በየሳምንቱ ከእያንዳንዱ የባህር ዳርቻ የውሃ ናሙናዎችን ይሰበስባሉ። ውሃው ባክቴሪያዎች እንዳሉት ይፈትሹታል። ሳይንቲስቶቻችን በማህበረሰብ ጤና ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ይመረምራሉ.። በውጤቶቹ ላይ ተመስርተን የሰዎችን ደህንነት ለመጠበቅ የባህር ዳርቻዎችን እንዘጋለን ወይም እንከፍታለን።

የውሃ ብክለት እንዳለ የሚጠቁሙ ባክቴሪያዎችን እንፈልጋለን። "የውሃ ብክለት" አብዛኛውን ጊዜ ከሰዎች፣ ከቤት እንስሳት ወይም እንደ ዝይ ካሉ የዱር አራዊት በሚወጣ ሰገራ ሲበከል ማለት ነው። ሰገራ ጀርሞችን ስለሚይዝ በአፍና በተቀረጡ የሰውነት ቆዳዎች ውስጥ ከገባ በሰዎች ላይ ህመምን ሊያስከትል ይችላል።

በዚህ ዓመት የባህር ዳርቻዎችን (beaches) የአዘጋግና የአከፋፈት ውሳኔዎችን እየለወጥን ነው። እነዚህ ለውጦች ዘመኑ ከደረሰበት ሳይንስ ጋር የተጣጣሙ ናቸው።

በኪንግ ካውንቲ የባህር ዳርቻዎች የሚዋኙ ከሆነ የባህር ዳርቻዎች የመዘጋት ምልክቶችን ቶሎ ቶሎ ሲቀያየሩ ሊያዩ ይችላሉ። ምልክቶቹ ለአጭር ጊዜ ሊቆዩ ይችላሉ። በአጠቃላይ ከዚህ በፊት ሲሰራበት በነበረው የውሳኔ አሰጣጥ ፕሮቶኮል መሰረት የባህር ዳርቻዎች ከዚህ በፊት ክፍት ሆነው የሚቆዩበትን የጊዜ መጠን ያህል ክፍት ይሆናሉ ብለን እንጠብቃለን።

## ለምን የማህበረሰብ ጤና ይህን ለውጥ አደረገ?

የባህር ዳርቻዎችን (Beaches) ለመዝጋት እና ለመክፈት የተጠቀምንባቸው መስፈርቶች ጊዜ ባለፈባቸው ሳይንሳዊ መመሪያዎች ላይ የተመሰረቱ ነበሩ። ወግ አጥባቂ የሆኑ ውሳኔዎችንም አስከትለዋል። የባህር ዳርቻን ለመዝጋት የውሃውን ብክለት ለማወቅ ብዙ ምርመራዎችን ማድረግ ይጠይቅ ነበር። ከዚያም የባህር ዳርቻን ለመክፈት ጥሩ የውሃ ጥራትን ለማሳየት ብዙ ምርመራዎችን ወስዷል።

አዲሶቹ መመዘኛዎቻችን በየሳምንቱ በምናገኘው አሁናዊ (real time) የውሃ ጥራት መረጃ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ስለዚህ በባህር ዳርቻ (Beaches) ላይ የውሃ ጥራት ሲጓደል የባህር ዳርቻው በፍጥነት ይዘጋል፤ የውሃው ጥራት ሲሻሻል ደግሞ የባህር ዳርቻው በፍጥነት ይከፈታል።

## ይህ ለእርስዎ ምን ማለት ነው?

የባህር ዳርቻዎች በፍጥነት ሊዘጉ እና እንደገና ሊከፈቱ ስለሚችሉ ለመጎብኘት የሚፈልጉት የባህር ዳርቻ ክፍት መሆኑን ለማወቅ የሃይቅ ዳርቻ ድረ ገፅን/ Lake Beach website ይጎብኙ (የቋንቋ አማራጮችን ያገኛሉ)።

ሁላችንም ውሃውን ከጎጂ ባክቴሪያዎች ነፃ እንዲሆን ማገዝ እንችላለን:-

- ዝይዎችን እና ዳክዬዎችን በባህር ዳርቻ ላይ አይመግቡ - እነሱን መመገብ የውሃውን ጥራት ያባብሰዋል።
- ከመዋኘትዎ በፊት ሁል ጊዜ ገላዎን ይታጠቡ።
- ህፃናት እና ታዳጊዎች ጥራት ያለው የመዋኛ ዳይፐር መልበሳቸውን ያረጋግጡ።
- የውሃ ጥራት ስጋቶችን ለአከባቢዎ ፓርኮች መምሪያ ሪፖርት ያድርጉ።

## በሚዋኙበት ጊዜ ደህንነትዎን ይጠብቁ

- የነፍስ አድን ጠባቂዎች ባሉበት ስፍራዎች ውስጥ ይዋኙ።
- በዚህ ወቅት ውሃው ቀዝቀዛ በመሆኑ ወደ ውስጥ ዘሎ መግባት ሰውነትዎ ከቅዝቃዜው የተነሳ አልታዘዝ ሊልዎት ይችላል። ይህም መስጠም እና ሞትን ሊያስከትል ይችላል - ምንም እንኳን ጠንካራ ዋናተኛ ቢሆኑም፤ በሐይቅ ወይም በወንዝ ውስጥ የሚዋኙ፣ የሚጫወቱ ወይም በጀልባ የሚሳፈሩ ከሆነ፣ የነፍስ አድን ጃኬትን ይልበሱ - በተለይም የነፍስ አድን ሰራተኛ ከሌለ።

- በአቅራቢያዎ የሚገኝ ተመጣጣኝ የህይወት አድን  ጃኬት ለማግኘት ይህንን ካርታ ይጠቀሙ (ይህ ድረ-ገጽ በእንግሊዝኛ ብቻ ነው)።
- ከኛ የውሃ ደህንነት ድረ-ገጾች (ይህ ድረ-ገጽ በእንግሊዝኛ ብቻ ነው) ስለ ዋና ደህንነት የበለጠ እወቁ/ተማሩ።